# አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚና

# የመለስ ራዕይ (ክፍል 3)

ዮናስ 11/17/12

ዛሬም የጥቅምት 2005 ዓ.ም ቅጽ 2 ቁጥር 7 "አዲስ ታይምስ" መጽሄት ጋር ነው ሙግቴ፡፡ "ኢህአዴግ ስንት ቦታ ሊሰነጠቅ ይችላል?" በተመስገን ደሣለኝ፣ "የሃይለማርያም የርዓዮተ - ዓለም ዕዳ" በሃይለመስቀል ሸዋም የለህ ከቀረቡት መጣጥፎች ጋር የማያስማሙኝን ሃሳቦች ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር አዋህጄ ሞግቼአለሁ።

በዛሬው መጣጥፌ አቻም የለህ ታምሩ እውነቱ የተባሉ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ መምህር በዚህችው መፅሄት ላይ “በኢትዮጵያ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ የተደቀነውና ያልታየው ትልቁ ፈተና” በሚል ርዕስ ካቀረቡት መጣጥፍ ላይ ያልተዋጡልኝን ሃሳቦችና ተሸፋፍነው የቀረቡና በተጨባጭ እውነታ ላይ ያልተመሰረቱ ሃሳቦችን መነሻ በማድረግ ከፀሃፊው ጋር ሳይሆን ከጽሁፋቸው ጋር እኔም በጽሁፌ እከራከራለሁ፡፡

“ዛሬ ያለው ባህላዊና አነስተኛ አርሶ አደርን ያስቀደመው ከምንጅላቶቻችን በቅብብሎሽ የወረስነው የእርሻ ኢኮኖሚ ስርዓት ላይ ተንተርሰን የሚጠበቀውን ያህል ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ስርዓት ማስፈን ወደማይቻልበት ደረጃ እየተቃረብን ይመስላል”፡፡ የሚል ማእከላዊ ጭብጥ ያለው የመቀሌው ዩኒቨርስቲ መምህር መጣጥፍ "ተልካሻ አስተሳሰብና አሰራር ይዘን ከባህር ጥልቀት በላይ ጥልቅ ከሆነው ድህነታችን ሊያወጣን ቀርቶ ስንዝር ሊያሻግረን አይችልም " ሲሉ የግብርናውን ፖሊሲና የልማት ዕቅዱን ይተቻሉ፡፡

በተለይም በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉበት ሀገር፣ የሚታቀደው እቅድ በአንድ የሥልጣን ዘመን ሊተገበር የታሰበ እቅድ ብቻ ነው መሆን ያለበት በማለት የሚሊኒየሙን የልማት ግብ እና የኢትዮጵያን ራዕይ ከእቅድ ጋር አምታተው አቅርበዋል፡፡

የመሬት ስሪት ፖሊሲው ደካማነት፣ ክፍለ ኢኮኖሚው በተፈጥሮ ቁጥጥር ስር የወደቀ መሆኑ፣ ተልካሻ የእርሻ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መተግበራቸው፣ ያልተጠኑ ስትራቴጂዎችና ፓኬጆች ለገበሬው መቅረባቸው፣ እርሻን ማእከል ያደረገ የመድን ዋስትና አለመኖር ከተዳሰሱት ችግሮች መካከል ዋነኞቹ እንደሆኑ የሚጠቅሱት መምህር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተወሰኑ ጥናታዊ ጽሁፎች እንደሚጠቁሙት (የእሳቸውን ጨምሮ) የኢትዮጵያ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ውጤታማ እንዳይሆንና ተራውን ለኢንዱስትሪው እንዳይለቅ የተጋረጠበት <u>በብዛት በጥናቶች ያልተዳሰሰው ፈተና</u> የቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማቋረጥ (Disadoption of Agricultural Technologies) ነው ይላሉ፡፡ ለዚህም የቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ማቋረጥ “ጥቂት ጥናቶችን” መሰረት ያደረገው ምክንያት የማስፉት ስትራቴጂ (Scaling up Strategy) ነው ሲሉም መምህሩ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

በዘፈቀደ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ አሰራሮችም እንዲሁ ለክፍለ ኢኮኖሚው ድቀት ምክንያቶች ናቸው ሲሉ የሚከራከሩት እኚሁ ኢኮኖሚስት የቴክኖሎጂ ግብአት ከራሱ ከአርሶ አደሩ ነጥቀን ወይንም ከባእዳን

ሽምተን በአርሶ አደሮች መካከል ያለው  ልዩነት ሳይጤን፣ ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ አስተሳሰብ፣ ንቃተ ህሊናና ባህሪ ጋር እንደሚሄድና እንደማይሄድ ግንዛቤ ሳይወስዱ፣ አርሶ አደሩ ያለበት የአየር ንብረትና የሚኖርበት መልክአ ምድራዊ ጠባይ ሳይተነተን ወዘተ. . . . ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ እርሻ በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲያድግ ለሚደረገው ጥረት በራሱ በቂ አይደለም ሲሉ ሃሳባቸውን ያጠናክራሉ፡፡

በተለይም የማስፋት ስትራቴጂው ላይ አጽንኦት በመስጠት ይህ አሰራር በአገር አቀፍ ደረጃ እየተመራንበት ያለ የእርሻ "ፖሊሲ" እንደሌለ የሚያሳብቅ ነው የሚሉት መምህር መሰረታዊ የእርሻ ግብአቶችና የተቀየጡ ምርጥ ዘሮች እንዲሁም አመች የሆነ የብድር አቅርቦትም በአርሶ አደሩ መንደር የለም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡

በእኔ አስተሳሰብ የእኚህ መምህር የትኩረት አቅጣጫና በቅቤ የተለወሰችው የመጣጥፋቸው ጭብጥ እንዲህ ሲሉ ያሰፈሯት ነጥብ ነች "አርሶ አደሩ ተጠቅሞ የሚያቋርጥበት ምክንያት ሳያምንበት በልዩ ልዩ ሰንካላ ምክንያቶች (መሬትህን ትነጠቃለህ፣ ማዳበሪያ አታገኝም፣ ቅጣት ይጣልብሃል) ወዘተ በሚሉ ማደናገሪያዎች) ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማስገደድ በአጭሩ እርሻ በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዳያድግ ትልቅ በር የሚከፍት ነው፡፡"

ሃሳቤ ትንሽም ብትሆን ጠቃሚ ናትና "በነፃ" መንግስት ይጠቀም ዘንድ ፈቅጃለሁ ብለው በስተመጨረሻ ተማጽኖ ያቀረቡት መምህር ትክክል አይደለህም የሚለኝም ካለ ይሞግተኝ ዘንድ ፈቃዴ ነው ባሉት መሰረት እነሆ አሁን ከዚህና ከላይ ካነሳሁት የመምህሩ ሃሳብ ጋር እሞግታለሁ፡፡

የሙግቴ ማዕቀፍ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሰራሽ የሆነው የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲውና የመለስ ራዕይ ሲሆኑ የክርክሬ መነሻ ግን የፀሐፊው እንደወረደ ያቀረቡት ሃሳብ ላይ ፊት ለፊት የፈጠጡ ስህተቶችን እና ተጠያቃዊ ያልሆኑት ሃሳቦች ላይ አስተያየት በመስጠት ነው፡፡

ፀሃፊው ተልካሻ የሚሉት የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ አሰራር እና ፍልስፍና 85 በመቶ የሚሆነው አርሶ አደርን ወደ ኢንዱስትሪ ማሸጋገር አይችልም ሲሉ በዝርዝር ወደኋላ ላይ ማስቀመጣቸው ላይቀር፣ በመግቢያቸው አካባቢ "ዛሬ ያለው ባህላዊና አነስተኛ አርሶ አደርን ያስቀደመው ከምንጅላቶቻችን በቅብብሎሽ የወረስነው የእርሻ ኢኮኖሚ ----" በማለት የጠቀሱት ሃሳብ ተቃርኖ ያለውና ልብ ያልተባለ የፀሃፊውን ዘፈቀዳዊነት የሚያመላክት ነው፡፡

የምንከተለው ፖሊሲ ግብርና መር የሆነ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ሆኖ ሳለ "እርሻ መር የኢንዱስትሪ ፖሊሲ" እያሉ መጥቀሳቸው በራሱ የፀሃፊውን ፍላጎት  የሚያሳብቅ ነው፡፡ ምክንያቱም እርሻን መሰረት አድርገው ስለ ኢንዱስትሪውና ስለኢትዮጵያ ማውራታቸው በመሰረቱ ስህተት  ስለሆነ-ስህተትነቱ የሚለካው ደግሞ እርሻ እና ግብርና ግልፅ የሆነ ልዩነት ያላቸው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ግብርና ሲባል አርሶ አደሩን አርብቶ አደሩን ጨምሮ እርሻውን፣ የእንስሳት ሃብት ልማቱን፣ የእርሻ ኢንቨስትመንቱን፣ የእንስሳት ሀብት ኢንቨስትመንቱን ወዘተ እና በአጠቃላይ የሰብል እና የእንስሳት ሃብት ልማትን የሚያጠቃልል ሰፊ አጀንዳ ሲሆን መንግስትም ይህን ሰፊ ጉዳይ በመሪነት ተጠቅሞ ወደ ኢንዱስትሪ የሚያሸጋግር ፖሊሲ የሚከተል መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል፡፡

እርሻ ማለት ደግሞ የሰብል ልማቱን ዘርፍ የተመለከተና በግብርና ውስጥ አንዱ ቅርንጫፍ ሲሆን በፀሃፊው አባባል መንግስት የሚከተለው ፖሊሲ "የሰብል ልማት ዘርፍን ብቻ መሪ ያደረገ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ መሆኑን ነው፡፡

ሌላው በግልጽ የሚታየው ስህተት ፀሃፊው ስለ እርሻ እያወሩ አርሶ አደር እና ገበሬ ሲሉ ቀላቅለው የሚያቀርቧቸው ስያሜዎች ሲሆን በተለይም አርብቶ አደሩን እና ሰፊ የሆነ የሀብት ምንጭ ያለበትን ክፍለ ኢኮኖሚ ወደ ጎን በመግፋት አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ከአንድ መምህር ለዚያውም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የኢኮኖሚክስ መምህር የማይጠበቅ ስህተት ነው፡፡

ሌላው በአርሶ አደሩ ጓሮ ስለ አርሶ አደሩ ንቃተ ህሊናና የግብአት አጠቃቀም ሲባል የተመደቡትን የልማት ሰራተኞች፤ ስለ አርሶ አደሩ ጤናና ጉልበቱን በማሳው ላይ የማሳለፍ ሰፊ ጊዜ ሲባል በየቀየው የተመደቡትን የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ስለ አርሶ አደሩ አቅም መጠናከር ሲባል በየወረዳው ያሉ የአነስተኛ ብድር አገልግሎት ተቋማትን እና የህብረት ስራ ማህበራትን የዘነጋው የመምህሩ መጣጥፍ የትኩረት አቅጣጫው የፖሊሲ ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ጉዳይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ይህ ሁሉ ስህተታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ "በነፃ" ተቀበሉኝ ያሉት መጣጥፍ መንግስትም ሆነ ለአርሶ አደሩ ተከፍሏቸውም ቢሆን እንደማያዋጣ ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ አረጋግጣለሁ፡፡

መምህሩ አንባቢያን ሳያደናገሩ ሊያጤኑትና አጽንኦት ሊሰጡት የሚገባው የመጀመሪያ ነጥብ በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የ20 አመት ከዚያ በላይ እድሜ ያለው የግብርና እቅድ አለማቀዱን ነው፡፡ ይልቁንም የኢትዮጵያን ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና ዘላቂነት ያለው ፖሊሲ ማዘጋጀት ከማናቸውም ስልጣን ከሚይዙ መንግስታት የሚጠበቅ ጉዳይ እንደ መሆኑ የሚሊኒየሙን ግብ ለማሳካትና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ሊያሰልፈን የሚችል ፖሊሲና ስትራቴጂ በሁሉም ዘርፍ ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ ማዋል እንዳለበት ታሳቢ በማድረግ ይህንን ፖሊሲና ስትራቴጂ በሁሉም ዘርፍ አዘጋጅቶ ስራ ላይ አውሏል፡፡

ይህ ፖሊሲ የትኛውም ፓርቲ በምርጫ አሸንፎ ስልጣን ቢይዝ ከሞላ ጎደል የሚሻሻለውን አሻሽሎ እና ከሚከተለው ርዕዮት ጋር የሚጣጣመውን ይዞ እንዲቀጥል በሚያስችል አኳኋን ሀገራዊ እና ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ አካቶ የተዘጋጀ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ራዕይም በ2020 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ መሰለፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተዘጋጀ ፖሊሲ ነው እንጂ ከመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ከስልጣን ኮንትራት ጋር የሚያያዝ እቅድ እንዳልሆነ ሊጤን ይገባል፡፡ ወደ ግብርናው ፖሊሲ ሳመራ ደግሞ አሁንም ትኩረቴ ግብርናውን እንጂ እርሻውን ለብቻ ገንጥዬ እንዳልሆነ እየገለጽኩ ነገር ግን በእርሻውም በኩል ተሟጋቹ የሚያነሱትን "ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ የማቋረጥ" ጉዳይና በምክንያት የተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የበለጠ ትኩረት በማድረግ ሃሳባቸውን በተጨባጭ እውነታዎች ላይ ተመርኩዤ እንደምሞግት ግንዛቤ እንዲያዝልኝ ጭምር ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ስናነሳ በመጀመሪያ መታየት የሚገባው ነጥብ የግብርናው ልማት መሰረታዊ አቅጣጫ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ዋናና መሰረታዊ ከሆኑት አቅጣጫዎች መካከል በመጀመሪያው ረድፍ ላይ የሚገኘው የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም የግብርና ልማት አቅጣጫ ነው፡፡

የመቀሌው መምህር ባህላዊና ከምንጅላቶቻችን በመቀባበል የወረስነው የሚሉት የእርሻ ዘይቤ ባህላዊነቱና የምንጅላቶቻችን ከመሆን የዘለለ የራሱ ሳይንሳዊ ምክንያት ያለው ዘይቤ ነው፡፡ 85 በመቶ የሚሆን የገጠር ነዋሪ ባለባት ሀገር ላይ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ የሚቻለው ካፒታልን በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ በመከተል ሳይሆን አገሪቱ ያላትን ሰፊ የሆነ የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ በመከተል መሆኑ የፍላጎትና የርዕዮት አለም ጉዳይ ሳይሆን የግብርና ሳይንስ ጉዳይ ነው፡፡

መንግስት የሰው ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የግብርና ልማት ስትራቴጂ እንከተላለን ሲል በእርሻ ማሳ ላይ ከሚፈሰው የሰው ሃይል በላይ ይሰማራል ማለቱ ሳይሆን ተፈላጊ በሆነው መጠን አሰማርቶ የሰው ሃይሉን የማምረት አቅም አሟጦ መጠቀምን የተመለከተ ነው፡፡ ይህመ ኋላቀር ቴክኖሎጂዎችን እና የግብርና ዘይቤዎችን እንከተል ማለቱ ሳይሆን የሰው ጉልበትን በመተካት ላይ ያላተኮረ የላቀ ቴክኖሎጂና የአስተራረስ ዘይቤ እንጠቀም ማለቱ ነው፡፡

የሰው ሃይልን በሰፊው በመጠቀም ዘመናዊ የግብርና ዘይቤዎችን በስራ ላይ ለማዋል ከሚያስችሉ ዋነኛ ስልቶች አንዱ ግብርናው የሰው ሃይሉን በማስተማርና በግብርና ሙያ በማሰልጠን የስራ ተነሳሽነቱን በማሳደግ የሚከናወን እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ እዚህ ላይ ዘመናዊ ማሽነሪ በሰፊው በመጠቀም በግብርና ሙያ ሰፊ ስልጠና የሌለውን ጥቂት ሰው ብቻ በማሰማራት ሊመጣ የሚችል የግብርና ልማት እንዳለ የሚያምነው የግብርና ልማት ፖሊሲ እንደዚህ አይነቱ የግብርና ልማት በሰፊ መሬት ላይ ጥቂት ሰው ብቻ በማሰማራት ሊመረቱ በሚችሉ የግብርና ምርቶች ላይ ያተኮረ የሰፋፊ እርሻዎች ግብርና (Extensive farming) ዘይቤ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በግብርና ሙያ በብቃት ያልሰለጠነ የሰው ጉልበትን የማይተኩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በአንድ ውስን ማሳ ላይ ሊገኝ የሚችለውን ምርት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመርና ከፍተኛ ዋጋ የሚያስገኙ የግብርና ምርቶችን በማምረት ላይ ያተኮረ የግብርና ዘይቤ (Intensive farming) መኖሩን በመግለጽ የእኛ ዋነኛ የግብርና ልማት አቅጣጫ የሰው ጉልበትን በሰፊው ለመጠቀም የሚያስችለው የግብርና ዘይቤ ላይ መሆኑን ያሰምርበታል፡፡

ከንቃተ ህሊናና ከአርሶአደሩ አቅም ጋር ተያይዘው ለቀረቡት የኢኮኖሚስቱ መከራከሪያዎች መነሻው "በተልካሻ አስተሳሰብ የተሞላው ፖሊሲ ነው" ቢባልም ፖሊሲው ግን ለዚህ መከራከሪያ ቁልጭ ያለ ምላሽ አስቀምጧል፡፡

በግብርና ስራ ላይ የተሰማራውን የሰው ሃይል በትምህርትና ስልጠና የላቀ ደረጃ ላይ በማድረስ፣ ይህ የግብርና ሙያው የዳበረ የሰው ሃይል የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና ስልቶችን እንዲጠቀም በማድረግ ላይ

ያተኮረ አቅጣጫ በማስቀመጥ፣ የመስኖ ልማትን፣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው የግብርና ምርቶችን፣ በውስን መሬት የላቀ የግብርና ምርት ለማስገኘት የሚችሉ አማራጮችን ሁሉ አሟጦ የመጠቀም የፖሊሲ አቅጣጫ መሆኑንም ይጠቁማል፡፡

የሰለጠነ የሰው ሃይልን ማዕከል ያደረገ የምርታማነትና የቴክኖሎጂ እድገት አቅጣጫን የመከተል ጉዳይ እንዲሆን በግልጽ በፖሊሲው ያሰፈረው መንግስት የግብርና ልማት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎቻችን በዚህ መሰረታዊ አቅጣጫ የሚመሩ መሆን እንዳለባቸውም አጽንኦት በመስጠት አስቀምጧል፡፡

"ባህላዊና ከምንጅላቶቻችን በወረስነው የእርሻ ዘይቤ ላይ ሆነን ያለአንዳች የተጠና ፖሊሲ ጥልቅ ከሆነው ድህነታችን ይቅርና ሸጥ እንኳ መሻገር አንችልም" ለሚለው የኢኮኖሚስቱ ትንታኔ የግብርና ልማት ፖሊሲያችን እንዲህ ሲል በግልጽ ምላሽ ይሰጣል፤የምንከተለው የግብርና ልማት አቅጣጫ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ በመጣ የግብርና ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሚቀጥል መሆኑን መጀመሪያ በመቀበል፤ አሁንም መምህሩ እንዳሉት ይህንኑ አቅም በማጣጣል ተንጠራርተን የተማረ አርሶ አደርና የላቀ ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅጣጫ እንከተል ብንል ከሁሉም ሳንሆን እንደምንቀር መራመድ የምንችለው አንድ እግራችንን በመሬት ላይ በማድረግ ብቻ የመሆኑን ሚስጥር በማስታወስ ያስቀምጣል፡፡

በመሆኑም ይህን ያልተማረ አርሶ አደር ሊደርስ የሚችልበት የላቀ ምርታማነት ደረጃ ላይ ለማድረስ፣ በልምድ ከተገኘው ወይም ከምንጅላቶቻችን ከወረስነው የግብርና ዘይቤ የበለጠውን በመምረጥና ይህንኑ በመጠኑ በማሻሻል በምርታማነታችን ላይ በጣም ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ያብራራል፡፡ ስለሆነም ነው የግብርናና የገጠር ልማት ስራችን በአንድ ጊዜ ሁለት ነገሮችን (ከትውልድ የተሸጋገረውን እና ወደሚቀጥለው የምርታማነትና የቴክኖሎጂ ደረጃ የሚያሸጋግረንን) መሰረት ያደረገ አቅጣጫ የሚከተለው፡፡

ሌላውና በመቀሌው ዩኒቨርስቲ መምህር የቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ የአግሮ ኢኮሎጅን መሰረት ያላደረገ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በሀገራችን ውስጥ በዝናብ መጠን፣ በመሬቱ አይነትና በአካባቢው ከፍታና በመሳሰሉት መስፈርቶች የሚለያዩ በርካታ የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች እንዳሉ ይታወቃል፡፡

መምህሩ እርሻውን ብቻ መነሻ ቢያደርጉም ትችታቸው ፖለቲካዊ በመሆኑ ምዘናዬ አጠቃላይ አገሪቱን የተመለከተ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በከብት ርቢ የሚኖሩ አርብቶ አደሮች የሚኖሩባቸው የምስራቁና በተወሰነ ደረጃም የደቡብ ቆላዎች፣ ሰፊ ያልታረሰ መሬትና ጥቂት ህዝብ የሚኖርባቸው ለእርሻ ስራ በጣም ምቹ የሆኑ የምዕራባዊ ክፍል ቆላዎች እና ብዙ ህዝብና ጠበብ ያለ የእርሻ መሬት ያላቸው ደጋማ አካባቢዎች እንዳሉ የሚገነዘበው መንግስት ለእያንዳንዱ አካባቢ የሚሆን ዝርዝር የልማት እቅድ አዘጋጅቷል፡፡እያንዳንዱ ሊያስመዘግብ የሚችለውን የላቀ እድገት እንዲያመጣ በማድረግ አጠቃላይ የአገራችን የግብርና ልማት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን የማድረግ የፖሊሲ አቅጣጫን እንደሚከተል በግልፅ አስቀምጧል፡፡

የመቀሌው ዩኒቨርስቲ ኢኮኖሚስት ምንም እንኳን በተደጋጋሚ እንደገለጹት ስለ እርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ውድቀት በምክንያትነት ያቀረቡት "ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ማቋረጥ እና የተለያዩ የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖችን

ታሳቢ ያላደረገ የቴክኖሎጅ ስርጭት" በእርግጥም ችግር ነው እንዳንል "ጥቂት" የጥናት ውጤቶችን መሰረት ያደረገ መጣጥፍ መሆኑን በተደጋጋሚ ገልፀውልናል፡፡

ሆኖም ግን በዚህ ረገድ የወቀሱት መንግስት ጤንነቱ የተጠበቀ፣ የስራ ፍላጎቱና ታታሪነቱ የተረጋገጠና በቂ ትምህርትና ስልጠና ያለው አርሶ አደር መፍጠር ለግብርና ልማታችን ወሳኙ መሰረት ቢሆንም ይህም ሃይል ሆኖ ያልተማረው አርሶ አደር ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚያስችለው የቴክኖሎጂ አቅርቦት ካላገኘ፣ ቴክኖሎጅውም በሚፈለገው መጠን ካልተባዛና በአግባቡ ወደ አምራች ካልተሰራጨ የሚፈለገው እድገት ሊገኝ እንደማይችል አምኖ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ብዛትና ስርጭትን የማሻሻል ጉዳይ የህዝቡን የማምረት አቅም ከማጎልበት ተግባር ጋር ተነጥሎ የማይታይ እንደሆነ አስምሮበት እየሰራ ነው፡፡

ቀደም ሲል በኢኮኖሚስቱም ሆነ በእኔ በኩል እንደተገለጸው በአገራችን እጅግ በርካታ የተለያዩ የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች አሉን፡፡ ስለሆነም ኢኮኖሚስቱ እንዳሉትም በሁሉም አካባቢዎች አንድ አይነት ቴክኖሎጂ መጠቀም ተገቢ አይሆንም፡፡ በአንድ አካባቢ የሚሰራ ቴክኖሎጂ (ለምሳሌ በቂ ዝናብ ባላቸው አካባቢዎች) በሌላ አካባቢ ለምሳሌ (በቂ ዝናብ በሌላቸው አካባቢዎች) ፈጽሞ እንደማይሰራ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡ ወይም ቢሰራም ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችል አይሆንም፡፡

በመሆኑም መንግስት በግብርና ልማት ፖሊሲው "ለተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚስማሙ መላውን የአገራችንን የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች ፍላጎት የሚያረኩ ቴክኖሎጅዎችን ማቅረብና ይህንኑ በቀጣይነት ማሻሻል ይኖርብናል" ሲል በግልጽ አስቀምጧል፡፡

በዚህ የማያበቃውና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ "ጥቂት" ጥናቶችን መሰረት አድርጎ ከድምዳሜ ላይ ለደረሰው "ተጠቅሞ የማቋረጥ" ጉዳይ ፖሊሲው የግብርና ቴክኖሎጂ አቅርቦት አንድ ጊዜ ተፈጽሞ የሚያበቃ እንዳልሆነና ቀጣይነት ያለው ፈጣን የግብርና ልማት ማረጋገጥ ከተፈለገ የማያቋርጥ የተሻሻለ የቴክኖሎጂ አቅርቦት መኖር እንዳለበት አጽንኦት በመስጠት ያብራራል፡፡

ኢኮኖሚስቱ "ተልካሻ" የሚሉትና ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ አንፃር ለቴክኖሎጂ አጠቃቀም ቦታ የለውም የሚሉትን ፖሊሲ አልተመለከቱት እንደሆነ እንጂ እንዲህ ይላል "የቴክኖሎጂ አቅርቦት ብዛትና ስርጭት ስርዓት ተፈጥሮና ቀልጣፋነትም ተረጋግጦ ቢሆን ዞሮ ዞሮ ይህንኑ ተቀብሎ ተግባራዊ የሚያደርገው አምራቹ አርሶ አደር ነው፡፡ ስለሆነም የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ አቅም ጋር እንዲመጥን ተደርጎ መቅረብ አለበት፡፡" አርሶ አደሩ ሊጠቀምበት የማይችል የተሻሻለ ቴክኖሎጂ እድገታችንን ከማፋጠን አንፃር ምንም ፋይዳ እንደማይኖረው ያስቀምጣል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ከስንት አመት አንዴ ብቅ የሚል ነገር ከሆነ እና በተከታታይና ያለማቋረጥ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች የማይቀርቡ ከሆነ የምንፈልገውን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ሊያረጋግጥልን እንደማይችል አስምሮበታል፡፡

ስለሆነም ቴክኖሎጂው ከተጠቃሚው አቅም ጋር መመጣጠን አለበት ሲል የሚገልጸው ፖሊሲ ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንፃር ሶስት የተለያየ አቅም ያላቸውን አርሶ አደሮች ታሳቢ ያደረገ አጠቃቀም ተግባራዊ መደረግ እንዳለበትም በግልጽ ያመላከተ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃና በዋነኝነት ያልተማረው አርሶ አደር ሲሆን በሂደት እየጨመረና ዋናው ክፍል እየሆነ የሚሄድ የተማረና የሰለጠነ አርሶ አደርም ስለሚኖር ሁለቱ አንድ ዓይነት ቴክኖሎጂ መጠቀም ስለማይችሉ ካልተማረው አርሶ አደር አቅም ጋር የሚመጣጠን የዝቅተኛ ቴክኖሎጂ ፓኬጅ መሰራጨት እንደሚኖርበት ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንና በሂደት በከፍተኛ ፍጥነት ይጨምራል ተብሎ ለሚገመተው የተማረ አርሶ አደር የሚቀርበው ቴክኖሎጂ የላቀና ላልተማረው ከሚቀርበው የተለየ መሆን እንዳለበት ከዚህም በላይ ሁሉም እንደ አቅማቸው የሚመጥናቸውን የቴክኖሎጂ አቅርቦት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ልዩ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ በኢኮኖሚስቱ በኩል ስህተት ናችሁና በነፃ ተማሩበት ከተባለው መጣጥፍ ቀደም ብሎ ከ15 ዓመት በፊት ፖሊሲው ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘና ኢህአዴግና በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የመለስን ራዕይ  የማስቀጠል ሚስጥር ስንፈትሽ ለመለስ ከድህነት በላይ አዋራጅ ነገር የሌለ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከዚህ በመነሳት ለኢኮኖሚስቱ በ"ጥቂት" የምርምር መነሻዎች የተሰጠ ድምዳሜ መለስ ቀደም ብሎ ምላሽ እንደሰጠ ማረጋገጥ እንችላለን፡፡

መለስ ከገጠር ልማት አኳያ በነደፈው የገጠር ልማት ስትራቴጂ ዋነኛ አቋሞቻችን ናቸው ያላቸው የአርሶ አደሩን ጉልበት መሬትና ውሃ በአግባቡ አቀናጅቶ በመጠቀም በአርሶ አደሩ ማሳዎች ላይ የግብርና ምርትና ምርታማነት በላቀ ደረጃ እንዲያድግ ያላሰለሰ ብቁ አመራር ሰጥቷል፡፡ ከዚህም አልፎ አርሶ አደሩ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ምርት ተላቆ ወደ ገበያ የሚቀርብ ምርት እንዲያመርት ያስቻለ አቅጣጫ ነድፎ ተግብሯል፡፡ አርሶ አደሩን እና የምርቱን ተጠቃሚዎች ከአቀባባዮች ብዝበዛ የማላቀቅ ዓላማ ያለውና በገጠርም በተስፋፋው የቴሌኮም አገልግሎት የታገዘ የግብይት ስርዓት እንዲፈጠር የላቀ አመራር ሰጥቷል፡፡

ምርጥ የተባሉትን የውጤት ተሞክሮዎች ለቅሞ በመያዝና እነርሱንም በማስፋፋት ዓላማ፣ ከክልል ፕሬዝዳንቶችና የግብርና ቢሮ ሃላፊዎች ጋር ቋሚ የግንኙነት ሥርዓት በመፍጠር የደከሙት ከተሻሻሉት እንዲማሩና የተሳካላቸው ገበሬዎችና የልማት አስፈፃሚዎች እውቅና የሚያገኙበት ስርዓት እንዲፈጠር ለማድረግ ያስቻለን የአመራር ጥበብ ተፈፃሚ አድርጓል፡፡

ሆኖም ግን የመቀሌው ኢኮኖሚስት የማስፋትን ስትራቴጂ "ከልምድ መለዋወጥና ከመማማር በዘለለ በተለያየ አግሮ ኢኮሎጂ ዞን ላይ ያሉት ሁሉ አንዳቸው የአንዳቸውን እንዲጠቀሙ የሚያስገድድ አሰራር ነው" ሲሉ ለተለየ የፖለቲካ ፍጆታቸው ሲሉ ከተጨባጩ እውነታ ሸሽተዋል፡፡

ፖሊሲውና አፈጻጸሙ ግን በግልጽ የተመለከተው ሆኖ ሳለ ኢኮኖሚስቱ "በማዳበሪያ ከማስፈራራት፣ ከመሬት ነጠቃ"ጋር በማያያዝ የፖለቲካ ቁማር ለመጫወት ይቃጣሉ፡፡ሆኖም ግን ረጋ ብሎ ከጨለምተኝነት አስተሳሰብ ወጥቶ ሁኔታውን ለመዘነው አገሪቱ እያስመዘገበችው ላለው ከፍተኛና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የአንበሳውን ድርሻ እያበረከተ ያለው ይህ በበሳልና በተጠና ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ የተቻለው የግብርና ፖሊሲና ስትራቴጂያችን ውጤታማነት ነው፡፡